የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

www.slttunhzb.net sh1@ttomar.net

———

ገ_ት-ድበ_20180805_ዐማርኛ

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የትንሣኤ ፡ እና ፡ የድል ፡ በዓል ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ መልእክት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡–

# « ***ዳግማዊ ፡ ዐድዋ !*** »

———

ለንደን ፥ ሚያዝያ ፡ 5 ፡ ቀን ፡ 2018 ፡ ዓ.ም. ።



የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !

**ቀዳማዊው ፡ የዐድዋ ፡ ድል ፥ የካቲት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ 1888 ፡ ዓ.ም. ፥ ከኢትዮጵያ ፡ እና ፡ ከአፍሪቃ ፡ ዐልፎ ፥ በመላ ፡ ዓለም ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ እኩልነት ፡ እንዲውን ፡ እና ፡ የቅኝ-ግዛት ፡ ሥርዐት ፡ ከሥር ፡ ከመሠረቱ ፡ ተናግቶ ፥ ከስድሳ ፡ ዓመታት ፡ በኋላም ፡ ፈራርሶ ፡ እንዲቀበር ፡ ያደረገ ፥ በሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ እና ፡ በሥልጣኔ ፡ ላቂያ ፡ የተገኘ ፡ የኢትዮጵያ ፡ እና ፡ የሀገራዊ ፡ ሕዝቧ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ድል ፡ ነው ።**

ዛሬ ፥ የዐድዋን ፡ ድል ፡ በዓል ፡ 130 ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡ ስናከብር ፥ ኢትዮጵያ ፡ ዳግመኛ ፡ በምልክዮሽ ፡ መዳፍ ፡ ውስጥ ፡ ወድቃ ፥ እግዚእናዋን ፡ ዐጥታ ፥ በሥልጣን ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ተዘፍቃ ፥ በሞት ፡ ሽረት ፡ ትግል ፡ ውስጥ ፡ ትገኛለች ።

የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ዐምሐራ ፥ በፋኖነት ፡ ተደራጅቶ ፥ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የሕይወት ፡ ዋጋ ፡ ሳይሣሣ ፡ እየከፈለ ፥ ሥልጡን ፡ ሀገሩን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሊታደጋት ፡ ተሰልፏል ። እሬቱ ፡ የገጠመው ፡ በእጅ-አዙር ፡ የሚዋጋ ፡ የሰንደቃዊ ፡ ምልክዮሽ ፡ (የ"ግሎባል ፡ ኢምፔሪያሊዝም") ፡ ኀይል ፡ ነው ። **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ በሕጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ የመመራት ፡ ሥርዐቱን ፡ እስካጣ ፡ ድረስ ፥ ለድል ፡ እንደማይበቃ ፡ ምልክዮሽ ፡ ስላረጋገጠ ፥ የኢትየጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ከሕጋዊ ፡ አመራር ፡ ማራቅን ፡ ዋነኛው ፡ የጥቃት ፡ ስልቱ ፡ አድርጎታል ።**

ደግመው ፡ ደጋግመው ፡ የሚነሡት ፡ የትግል ፡ ቡድኖች ፡ ኹሉ ፥ ወይ ፡ በባዕድ ፡ "አይዲዮሎጂ" ፡ የሰከሩ ፡ ፍሬ-ቢሶች ፣ ወይ ፡ በ"ክልል" ፡ የጠበቡ ፡ ስኡኖች ፡ እየኾኑ ፥ የዐድዋ ፡ ፍሬዎች ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እየተበሉ ፥ ምልክዮሽ ፡ እና ፡ ግብር-ዐበሮቹ ፡ ምንም ፡ ሳይሠጉ ፥ እንሆ ፥ ለ 50 ፡ ዓመታት ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ የማፈራረስ ፡ ርኩስ ፡ ግብራቸውን ፡ ቀጥለዋል ።

ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ ይህን ፡ የጥፋት ፡ አካኼድ ፡ ጠቀሜ ፡ በማመልከት ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሕጋዊ ፡ አንድነታዊ ፡ ሥልጣኑን ፡ በፍጥነት ፡ እንዲያበጅ ፡ እና ፡ እንዲድን ፡ ኀምሳ ፡ ዓመታት ፡ ሙሉ ፡ መልእክቱን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሲያስተላልፍ ፡ ቈይቷል ። በተፈለገው ፡ ፍጥነት ፡ አልተሰማም ፤ ማወራኛውም ፡ ቢኾን ፥ መልእክቱን ፡ ለመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለማድረስ ፡ አልተባበረውም ።

ለሀገር ፡ ህልውና ፡ እስከ ፡ ኾነ ፡ ድረስ ፥ ለ 50 ፡ ዓመታት ፡ ይቅርና ፥ ለ 5000 ፡ ዓመታትም ፡ ሳይሰለቹ ፡ በወተወቱ ። ምልክዮሽ ፥ በጥፋት ፡ ዐቅዱ ፦ *"የኹለት ፡ ትውልድን ፡ ናላ ፡ በከፋፋይ ፡ ስብከት ፡ ከሰበክኹት ፡ ወዲያ ፥ የአንድነት ፡ ዐርበኝነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ አይታሰብም !"* ፡ ብሎ ፡ ነበር ።

**ዳሩ ፡ ግን ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ! ልጅኽ ፡ ፋኖ ፡ የዐርበኝነቱን ፡ ፈር ፡ ተልሞልኻል ! ሥልጣኔኽን ፡ አንግበኽ ፥ ይህን ፡ የሰንደቃዊ ፡ ምልክዮሽን ፡ የጥፋት ፡ ዐቅድ ፡ ዳግመኛ ፡ ለማምከን ፡ ለዳግማዊ ፡ ዐድዋ ፡ ተነሣ ! ስትነሣም ፥ እግዚአብሔር ፡ ይረዳኻል ❖**

ትሑት ፡ አገልጋይኽ ፥

ኢ.ሀ.ሥ.አ. ።

**እግዚአናችንን ፡ የማስከበር ፥**

**ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥**

**ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡**

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ **ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!**

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

**ሥልጡንሕዝብና ።**

**www.slttunhzb.net**